# COVID-19 ይዞኝ ከነበረ

# መከተብ ያስፈልገኛል?

መከተብ ለእርስዎ ሌላ ተጨማሪ የመከላከያ ሽፋን ይጨምርልዎታል። እርስዎ አስቀድመው ተይዘው የሚያውቁ እንኳን ቢሆን፣ ክትባቱ የሰውነት የበሽታ መከላከልን የሚያጠነክር እንደ አምጣቂ ሆኖ ያገለግላል።



## ስለ COVID-19 ትክክለኛ ወሬ

### እራስዎን፣ ቤተሰብዎን እና ታካሚዎችዎን ይጠብቁ

አስቀድመው ተይዘው የሚያውቁ ቢሆንም እንኳን የ COVID-19 ክትባት ያስፈልግዎታል።

- ለሁለተኛ ጊዜ በ COVID-19 የሚያዙ ሰዎች እንዳሉ ሪፖርቶች አሉ፣ ይህም መከተብን የበለጠ አስፈላጊ እንዲሆን አድርጎታል።
- በክትባቱ የሚገኘው የመከላከል ዓቅም በኢንፌክሽኑ ምክንያት ከሚገኘው ዓቅም የበለጠ ጠንካራ ነው። ኤክስፐርቶች በኢንፌክሽኑ በመያዝ ምክንያት የሚገኘው የመከላከል ዓቅም ምን ያክል ጊዜ እንደሚቆይ ወይም አዳዲስ ዝሪያዎች ላይ ሊሰራ የሚችል ስለመሆኑ አያውቁም።
- መከተብ አሁን እየመጡ ካሉት ዝሪያዎች ይጠብቅዎታል።

### ማወቅ ጥሩ ነው

- ለ COVID-19 ኢንፌክሽኑ በተወሰኑ ዓይነት መድሃኒቶች ህክምና ተደርጎሎት ከሆነ፣ ለመከተብ መጨረሻ ከታከሙበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ 90 ቀናት መቆየት አለብዎ። ለበለጠ መረጃ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።.
- በአሁን ወቅት በቫይረሱ ከተያዙ ወይም ምልክቶችን ካዩ የCOVID-19 ክትባት መከተብ የለብዎትም። ለመከተብ አስተማማኝ የሆነበትን ጊዜ ለማወቅ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነገግሩ።

**ነጻ ክትባትዎን ያግኙ!**

የበለጠ ይማሩ በ VDH የታካሚ ትምህርት - የክትባት መረጃ (vdh.virginia.gov/covid-19-vaccine/patient-education/)

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH